## 7 የደንጊ ትኩሣት በሽታ መካላከያ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?

1. የትንኝ መራቢያ ቦታዎችን ማፋሰስና እንዲደደረቅ በማድረግ የአካባቢ ቁጥጥር ሥራን አጠናክሮ መስራት፣
2. በበሽታው የተያዘው ሰው በሽታውን በትንኝ ንክሻ አማካኝነት ወደ ሌላ ሰው እንዳያስተላልፍ ቀንም ሆነ ማታ አጐበር ውስጥ መተኛት፣ ጤናማውም ሰው ቢሆን ሁሌ በሚተኛበት ጊዜ አጐበር መጠቀም አለበት፡፡
3. ትንኝን ለማባረር የሚያገለገሉ የቆዳ ቅባቶችን መጠቀም
5. በህብረተሰቡ ውስጥ የተጠናከረ አሠሣ ማድረግና ህብረተሰቡን ስለበሽታው ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
6. ሪፖርት ማድረግ - በአንድ አካባቢ የድንጊ ትኩሣት በሽታ መኖሩ ከተጠረጠረ በክልሉ ለሚገኙ መንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም በአቅራቢያው ላሉ ጤና ድርጅቶች ማሣወቅ፣

## 8 የደንጊ ትኩሣት በሽታ ሲገኝ ወይም ሲጠርጠር ለማን ሪፖርት ይደረጋል?

ማንኛውም ሰው ድንገተኛ የሆነና ከፍተኛ ትኩሳት ካለበት በአፋጣኝ ወደ ጤና ድርጅት እንዲሄድ በማድረግ በአካባቢ ላለ ጤና ድርጅትም ሆነ መንግስታዊ መዋቅር ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

አንድ ታማሚ የደንጊ ትኩሣት በሽታ መታመሙ በላቦራቶሪ ከተረጋገጠ በሽተኛዉ ባለበት አካባቢ ወረርሽኝ መከሰቱን ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩን ለሚመለከታቸዉ አካላት በአስቸኳይ ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

## 9 ጠቃሚ ምክሮች

1. አካባቢን ለትንኝ መራቢያ ምቹ እንዳይሆን ያድርጉ
   - ያቆሩ ውሐማ አካላትን ማፍሰስና መድፈን
   - በማይደፈኑ ውሃማ አካባቢዎች የአቤት ኬሚካል/ ቴሞፎስ/ በመጠቀም ትንኝ እንዳይራባ ማድረግ
2. የቤት መስኮትን በወንፊት በመጋረድ ትንኝ ወደቤት እንዳይገባ ይከላከሉ
3. የህመም ስሜት ሲሰማዎ ፈጥነው ወደ ጤና ድርጅት በመሄድ ባለሙያ ያማክሩ
4. የታመመ ወይም የሞተ ሰው ሲኖር በቶሎ ለጤና ባለሙያዎች ሪፖርት ያድርጉ


## ስተጨማሪ መረጃ በሚከተሉት ይጠቀሙ

**የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ማዕከል**

**Tel:** +251 11 275 8631
+251 11 276 5340

**Fax:** +251 11 275 8634

**Email:** PHEMcenter@ehnri.gov.et

**Website:** http://www.ehnri.gov.et


World Health Organization

unicef



# የደንጊ ትኩሳት በሽታ

## 1 የደንጊ ትኩሣት በሽታ ምንድን ነው?

የደንጊ ትኩሣት በሽታ በድንገት በመነሣት ከፍተኛ ትኩሣት የራስምታት በተለይም ከዓይን ጀርባ በኩል የሚሠማ ከባድ ህመም፣ የመገጣጠሚያና የጡንቻ ሕመም ብሎም ሽፍታ፣ ነስርና ድድ መድማት የሚያስከትል በትንኝ ንክሻ የሚተላለፍ በሽታ ነው፡፡

## 2 የደንጊ ትኩሳት በሽታ ሥርጭቱ ምን ይመስላል?

የደንጊ በሽታ በዓለም ላይ በምድር ወገብ አካባቢ ባሉ ሞቃታማ አካባቢዎች፦ በአፍሪካ፣ ላቲንና ሰሜን አሜሪካና የደቡብ ምስራቅ እስያ አካባቢዎች በስፋት ተሠራጭቶ የሚገኝ ሲሆን በአጠቃላይ 2.5 ቢሊዮን ያህሉ የዓለም ህዝብ ለበሽታው ተጋላጭ በሆኑት አካባቢዎች ይኖራሉ።

ከሠሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሃገሮች በሽታው በስፋትና በወረርሽኝ መልክ እየተከሠተ መታየቱ ተመዝግቧል።

ሀገራችን ካለችበት የመልክአ ምድር አቀማመጥ የተነሳ ለበሽታው መተላለፊያ ለሆኑ ትንኞች ምቹ ብትሆንም እስካሁን ድረስ በሽታው በሃገራችን ደረጃ ተከስቶ አያውቅም።

## 3 የደንጊ ትኩሳት በሽታ መንስኤዎችና የመተሳሰፊያ መንገዶች ምን ምንናቸው ?

የደንጊ ትኩሣት በሽታ መንስኤ በትንኝ ንክሻ የሚተላለፍ በዓይን የማይታዩ ረቂቅ ተህዋስያን ቫይረስ ሲሆኑ የበሽታው አስተላላፊ ትንኝም እንደማንኛው የወባ ትንኝ ዝርያ ሲሆን ቫይረሱን ከታመመ ሰው ወደ ጤናኛ ሠው በማስተላለፍ በሽታው በወረርሽኝ መልክ እንዲከሰት ወሳኝ ሚና ይጫወታል ይህ የትንኝ ዝርያ በአብዛኛው በቀን በምሽትና ንጋት ላይ ሰዎችን ይነክሣል።



የደንጊ በሽታ በሰዎች ንክኪ አይተላለፍም።

## 4 ለበሽታው የሚያጋልጡ ነገሮች ምንምን ናቸው?

በሽታውን አስተላላፊ ትንኝ በአካባቢ መኖሩ፣ የበሽታው መከሠት፣ ለትንኝ መራቢያ ምቹ የሆኑ አካባቢየዊ ሁኔታዎች /ያቆሩ ውሃዎች፣ ቦይ፣ ውሃ ሊይዙ የሚችሉ እንደ ጐማ፣ ሽክላ፣ ቆሪኪ ወዘተ/ ለትንኝ ንክሻ የተጋለጠ አለባበስ እና የመሣሠሉት ናቸው።

## 5 የድንጊ ትኩሣት በሽታ ዋና ዋና ምልክቶች ምን ምን ናቸው ?መቼ ይከሠታሉ ?

አንድ ሰው በሽታው ሊያስተላልፍ በሚችል ትንኝ በተነከሰ ከ4 እስከ 10ቀናት ውስጥ የሕመም ስሜቶችና ምልክቶችን ማሣየት ይጀምራል። የበሽታው ዋና ዋና ምልክቶችን በሁለት እርከን ከፍሎ ማየት ይቻላል።

በመጀመሪያው ደረጃ- በዋናነት ትኩሳት ሲሆን - ከ2 እስከ 7 ቀን የሚቆይ ከፍተኛ ትኩሣት፣ ብርድ ብርድ ማለትና ማንቀጥቀጥ፣ የጡንቻና የመገጣጠሚያ ቁርጥማትና ህመም፣ ራስምታት በተለይም ከአይን ጀርባ የሚሰማ ህመም፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ/ ማጣትና የድድና አፍንጫ መድማት እና ወዘተ ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ሊከሠት የሚችል ምልክቶች የደንጊ የመድማት ችግር የሚያስከትል ትኩሣት በሽታ በመባል ይታወቃል። እነዚህም፡- ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች እንዳሉ ሆነው

- ትኩሳቱ እየቀነሰ ሲሄድ ተከታታይ የሆነ ትውኪያ፣ ከፍተኛ የሆድ ሕመም፣ ትንፋሽ ማጠርና ለመተንፈስ መቸገር ሲሆኑ፣ በዚህ ወቅትም ከፍተኛ የደም ግፊት መቀነስና (Shock) የደም ዝውውር መዛባት ችግር በመፍጠር ለሞት ሊዳርግ የሚችል አደገኛ ሁኔታ ይከሰታል። በዚህ ወቅትም ከአፍንጫ፣ ከድድ፣ ከቆዳ አካባቢና እንዲሁም ከውስጥ አካልም የመድማት ችግር ሊፈጠር ይችላል።

- እነዚህ ምልክቶች መታየት ሲጀምሩ ወደያውኑ የሕክምና እርዳታ ካልተደረገ የሞት አደጋ ሊያስከትል ይችላል።

## 6 የደንጊ ትኩሣት በሽታ ምርመራና ሕክምናው ምንድን ነው?

ከላይ የተጠቀሱት የደንጊ በሽታ ምልክቶችና ስሜቶች የተሠማው ሰው ወዲያውኑ ፈጥኖ ወደ ጤና ድርጅት በመሄድ አስፈላጊውን የባለሙያ ምክርና ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል። የደንጊ በሽታ በቀላሉ በሕክምና ሊረዳ የሚችል በሽታ ሲሆን በበሽታው የተያዘ ሰው ቶሎ የምርመራና የሕክምና ዕርዳታ ካላገኘና ከዘገየ ግን ለሕልፈተ ሕይወት ሊዳርግ ይችላል።

የበሽታው ምልክት የታየበት ሰው የሕመም ማስታገሻ መውሰድ በቂ ዕረፍት ማድረግና በርካታ ፈሳሽ እየወሰደ የጤና ባለሙያ ማማከር ይኖርበታል።

**ማስታወሻ፡-**
በዚህ በሽታ የተጠረጠረ ሰው አስፕሪን እንዲወስድ አይመከርም፣ መውሰድም የለበትም።